# ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስት ሴክሬተሪያት
# የተሰጠ መግለጫ

የሚኒስትሮች ም/ቤት መስከረም 28 ቀን 2009 ዓ.ም. በመላው ሃገራችን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲታወጅ ካደረገ በኋላ አዋጁን ለማስፈፀም የሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማትን በአባልነት ያቀፈ የኮማንድ ፖስት ተቋቁሟል።

የኮማንድ ፖስቱ ተደራጅቶ የሃገሪቱ የፀጥታ ሀይሎች በአንድ ኮማንድ ስር እንዲሆኑ በማድረግ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በፈፃሚ አካላት ዘንድ በየደረጃው ተገቢውን ግንዛቤ እንዲፈጠር ከተደረገ በኋላ የአፈፃፀም መመሪያ በማፅደቅና እቅድ በማዘጋጀት በፍጥነት ወደ ስራ ገብቷል።

በዚሁም መሰረት ከማእከል ጀምሮ በተለያየ ደረጃ የተቋቋሙት የኮማንድ ፖስቶች በሰላም ወዳዱ ህዝባችን የላቀ ድጋፍና ትብብር እየታገዙ እስከአሁን ድረስ ባካሄዱት እንቅስቃሴ ከተገኙት ውጤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹን ብቻ ለመጥቀስ ያህል፦

- በአስቸኳይ ጊዜ እርምጃ አፈፃፀም መመሪያ አንቀፅ 31 መሰረት
  - በአማራ ክልል በሰሜን ጎንደር ከጎንደር ከተማና አከባቢው ሸፍተው ጫካ የገቡና ከአሸባሪ ሀይሎችና ታጣቂዎች ጋር ሲገናኙ ከነበሩት ውስጥ በአከባቢው ህዝብ ድጋፍና ትብብር 93 ሰዎች በአከባቢው ለሚገኝ የፀጥታ ሀይል እጃቸውን ሰጥተው የገቡ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 45 ከነሙሉ ትጥቃቸው 38 ደግሞ ያለ ትጥቅ የገቡ ናቸው፣

  - በኦሮሚያ ክልል ቄሌም ወለጋ ዞን በደንቢደሎ ከተማና ሰዶ ወረዳ ዙርያ ከተለያዩ ቦታዎች ተዘርፈው የተወሰዱ በቁጥር 70 የሚደርስ የጦር መሳርያ በራሳቸው በዘራፊዎቹና በህብረተሰቡ ጥቆማ ለፀጥታ ሀይሎች አስረክበዋል፣

  - በዚሁ በቄሌም ወለጋ ዞን ተፈጥሮ የነበረውን ሁውከትና ብጥብጥ ሲመሩና ሲያስተባብሩ ከነበሩት መካከል በአካባቢው ህዝብ የማያቋርጥ የማጋለጥና የጥቆማ ስራ አስከአሁን 110 ሁከተኞች በቁጥጥር ስር ውለው ለጊዜው ተደብቀው የቀሩትን ሁከተኞች ለመያዝ የክትትል ስራው ተጠናክሮ ቀጥሏል፣

- በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ አርሲ ዞን በተፈጠረው ሁከትና በህዝብ ንብረትና የልማት ተቋማት ላይ በደረሰው ከፍተኛ ውድመት ላይ ግንባር ቀደም ተሳታፊ ከነበሩት መካከል በህዝቡ ትብብርና ጥቆማ በሻሸመኔ ከተማ 450 እና በምዕራብ አርሲ የተለያዩ ወረዳዎች 670 በድምሩ 1120 ተጠርጣሪዎች በህግ ቁጥጥር ስር ውለው ጉዳያቸው በመጣራት ላይ ይገኛል፣

- በዚሁ በምዕራብ አርሲ ዞን ሻሸመኔ ከተማን ጨምሮ በተከሰተው ሁውከትና ብጥብጥ በሁውከተኞች ከተዘረፈው 162 የጦር መሳርያ ውስጥ በአገር ሽማግሌዎች ጥረትና በራሳቸው በሁውከተኞቹ በጎ ፈቃድ ከተዘረፈው የጦር መሳርያ ውስጥ እስከአሁን ድረስ 88 ያህሉ የተመለሰ ሲሆን የቀረውን ለማስመለስ ጥረቱ ተጠናክሮ ቀጥሏል፣ ለጊዜው መጠኑና አይነቱ ያልታወቀ ከተለያየ የመንግስት፣ የግልና የልማት ተቋማት የተዘረፈ ብዛት ያለው ንብረትም የማስመለስ ስራ እየተሰራ ይገኛል፣

- በምዕራብ ጉጂ ዞን ከተዘረፉ የጦር መሳሪያዎች መካከል በህዝብ ጥቆማና የማጋለጥ ስራ 32 ክላሽ የጦር መሳርያዎች እንዲሁም ከተለያዩ የህዝብ ተቋማት በሁከተኞች ተዘርፈው የነበሩ ኮምፒተሮች፣ ሞተር ሳይክሎች የቢሮ ቁሳቁሶች...ወዘተ የማስመለስ ስራ የተካሄደ ሲሆን የሁከቱ አስተባባሪና ግንባር ቀደም ተሳታፊ ከነበሩት መካከል በአከባቢው ህዝብ ጥቆማና የማጋለጥ ስራ እስከአሁን 302 ተጠርጣሪዎች በህግ ቁጥጥር ስር ውለው ጉዳያቸው እየተጣራ ሌሎች 20 የሚሆኑ የሁከቱ አስተባባሪዎች ደግሞ በአዋጁ የአፈፃፀም መመሪያ የጊዜ ገደብ መሰረት በፈቃዳቸው እጃቸውን ለመስጠት ከሃገር ሽማግሌዎች ጋር እየተነጋገሩ ይገኛል፣

- በምዕራብ ሸዋ ዞን በአዳማ፣ ቦራ፣ ሎሜ ሊበን ጭቋላ፣ አደአ፣ ቦስትና አዳሚ ቱሉ በተባሉ ሰባት ወረዳዎች በተፈጠረው ሁውከት ከተለያዩ የፀጥታ አካላት፣ ግለሰቦችና ተቋማት የተዘረፉ የጦር መሳርያዎች ውስጥ በህዝቡ ጥቆማና ፍተሻ እስከአሁን 92 ዘመናዊና ኋላቀር የጦር መሳርያዎችና 8 ሽጉጦች የተሰበሰበ ሲሆን የሁከቱ ቀንደኛ መሪዎች በቁጥጥር ስር ለማዋል የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ ቀጥሏል፣

- በአጠቃላይ በኦሮሚያ ክልል ከተለያዩ አካላት ከተዘረፈው በድምሩ 513 የተለያየ አይነት የጦር መሳርያ ውስጥ እስከአሁን ድረስ በተደረገው እንቅስቃሴ 384 ያህሉ ተመልሷል፣

* በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.መንግስት የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት *

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ቁጥር 3
The Federal ... Republic ... Office No.3

- በአስቸኳይ ጊዜ እርምጃ አፈፃፀም መመሪያ አንቀፅ 4 ለህዝብ አገልግሎት አለመስጠት የሚለውን ድንጋጌ በመተላለፍ
    - በአማራ ክልል በጎንደር ከተማ የንግድ ሱቆቻቸውን በመዝጋት አገልግሎት ለማቋረጥ የተንቀሳቀሱ 13 የሚሆኑ ጥቂት ነጋዴዎች፣ የስራ ማቆም አድማ እንዲደረግ ውስጥ ውስጡን ሲቀሰቅሱ የነበሩ ሌሎች 13 ተጠርጣሪዎች፣ እንዲሁም ከትምህርት ገበታ ሆን ብለው በመቅረት የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማደናቀፍ የሞከሩ 3 አስተማሪዎች ህብረተሰቡ በሰጠው ጥቆማ በቁጥጥር ስር ውለው ጉዳያቸው እየተጣራ ይገኛል፣

    - በተመሳሳይ ሁኔታ በአማራ ክልል በባህርዳር ከተማ የንግድ ሱቆቻቸውን በመዝጋት አገልግሎት ለማቋረጥ የተንቀሳቀሱና ህዝቡ በሰጠው ጥቆማ በቁጥጥር ስር ከዋሉት 35 ነጋዴዎች መካከል 6ቱ ጉዳያቸው ተጣርቶ ሲለቀቁ፣ የቀሩት 29 የንግድ ተቋማቱ ባለቤቶች ጉዳያቸው እየተጣራ ይገኛል፣

በአጠቃላይ ባለፉት ጥቂት ወራት ሁከት በተቀሰቀሰባቸው አንዳንድ የሃገራችን አከባቢዎች የህዝብን ሰላም በማወከና የግልና የህዝብ የልማት ድርጅቶችና የኢንቨስትመንት ተቋማትን በማውደምና በመዝረፍ የተሳተፉ ብዛት ያላቸው ተጠርጣሪዎች በአዋጁ የአፈፃፀም መመሪያ መሰረት በራሳቸው ፈቃድና በህብረተሰቡ ጥቆማና የማጋለጥ ስራ በቁጥጥር ስር እንዲውሉ በማድረግ ጉዳያቸው እየተጣራ ሲሆን በየደረጃው በተቋቋሙት የኮማንድ ፖስቶች ከህዝቡ በሚያገኙት ጥቆማና ድጋፍ የጦር መሳርያን ጨምሮ የተዘረፉ በርካታ የግልና የህዝብ ንብረቶች የማስመለሱ ስራ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

የሰላሙና የልማቱ ዋነኛ ተጠቃሚ የሆነው ህዝባችን የጥፋት ሀይሎችን እኩይ ድርጊት ከማከሸፍ አልፎ በየደረጃው ለተቋቋሙ የኮማንድ ፖስት አካላት መረጃ በማቅረብና ተጠርጣሪ ወንጀለኞችን በማጋለጥና አሳልፎ በመስጠት ለአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ተፈፃሚነት ባሳየው ቁርጠኝነት በአሁኑ ወቅት በሁሉም የሃገራችን አከባቢዎች ሰላም ለማስፈን ማስቻሉን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስት ሴክሬተሪያት በከፍተኛ አድናቆት እየገለፀ ለሰላም ወዳዱ ህዝባችን ያለውን የላቀ ክብርና ምስጋና በዚህ አጋጣሚ ለመግለፅ ይወዳል፡፡

ህዝቡ ያነሳቸው የመልካም አስተዳደርና የልማት ጥያቄዎችን ለመፍታት በቅድሚያ በመላው ሃገራችን አስተማማኝ ሰላም ማረጋገጥ ወሳኝ በመሆኑ ከዚህ አንፃር ህብረተሰቡ ሰው የገደሉ፣ ማንኛውም ንብረት ያቃጠሉና የዘረፉ ተጠርጣሪ ወንጀለኞችን አሳልፎ በመስጠትና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁንና የአፈፃፀም መመሪያው ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀሙ ሰዎችን በየደረጃው ለተቋቋሙ የኮማንድ



የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Government Communication

ፓስቶች መረጃ በማቅረብ የጀመረውን ንቁ ተሳትፎና ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪያውን በድጋሚ ያቀርባል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ባለፈው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ በአንዳንድ የሃገራችን አከባቢዎች በተቀሰቀሰው የህውከት እንቅስቃሴ ላይ በቡድን ወይም በግል የተሳተፈ፣ የጦር መሳርያ ወይም ማንኛውንም የግልም ሆነ የመንግስት ንብረት የዘረፈ፣ ለህገወጥ ተግባራት የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ያደረገ፣ ወረቀት በመበተን አድማ በማድረግ የተሳተፈና ያነሳሳ፣ እንዲሁም ሰው የገደለ፣ ማንኛውንም ንብረት ያቃጠለና ወንጀል የፈፀመ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የእርምጃ አፈፃፀም መመሪያው አንቀፅ 31 መሰረት የተሰጠው የጊዜ ገደብ ከማለቁ በፊት በቀሩት 5 ቀናት ውስጥ በአቅራቢያው ለሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ እጁን እንዲሰጥና የዘረፈውንም ንብረት እንዲመልስ በጥብቅ ያሳስባል፡፡

**የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስት ሴክሬተሪያት**

**ጥቅምት 9 ቀን 2009 ዓ.ም.**
**አዲስ አበባ**